የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሰላሳኛ ዓመት ቁጥር ፯ አዲስ አበባ
ህዳር ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.7
ADDIS ABABA , 23rd November 2023

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፫/፪ሺ፲፮

ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተቀናጀ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፲፭ሺ፪፻፹

**Content**

Proclamation No. 1303/2023

Italian Republic Loan Agreement for Financing Support for the Operationalization and Sustainability of For Integrated Agro-industrial Parks in Ethiopia Project Ratification Proclamation …………………………….……………Page 15280

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፫/፪ሺ፲፮**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተቀናጀ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሃያ ሁለት ሚሊዮን ዩሮ (፳፪ ሚሊዮን ዩሮ) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ

**PROCLAMATION NO. 1303/2023**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF ITALIAN REPUBLIC**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic Government of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Twenty Two Million Euro (Euro 22,000,000.00) for financing Support for the Operationalization and Sustainability of Integrated Agro-industrial Parks in Ethiopia Project, was signed in Addis Ababa on 17th day of January, 2023;

**WHEREAS**, the House of Peoples'

ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ፫ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፩ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተቀናጀ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፫/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር F.ROT/AID 20/003/00 በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሀያ ሁለት ሚሊዮን ዩሮ (፳፪ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

Representatives of The Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 3rd year working period, 1st ordinary session held on 12th Day of October, 2023;

**NOW,THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Italian Republic Loan Agreement for Financing Support for the Operationalization and Sustainability of Integrated Agro-industrial Parks in Ethiopia Project Ratification Proclamation No. 1303/2023".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number F.ROT/AID 20/003/00 signed in Addis Ababa on 17th day of January, 2023 between The Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan an amount equivalent to Twenty Two Million Euros (Euro 22,000,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 23rd Day of November ,2023**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**